EthioLion

**ለክቡር አቶ ኀይሉ ሻውል - የመኢአድ ሊቀ መንበር**

**አዲስ አበባ**

ስፐቴምበር ስምንት ሁለት ሺህ ስምንት ዓ.ም

ክቡር ሊቀመንበር፤

ቅንጅት የሚለውን አርማ አንግበው ፓርቲያችንን በመምራት ወገኖን ከወያኔ አስከፊ አገዛዝ ለማላቀቅ ሲታገሉበት እና ሲያታግሉበት እስከ እስር ቤትም ድረስ የተማገዱበት ቢሆንም፤ ይሄ የኢትዮጵያን ህዝብ በአንድነት ያስተቃቀፈ አርማ ያስፈራው ወያኔ በውስጣችን ተሰግስገው የነበሩ ከሃዲዎችን በመጠቀም ከኢትዮጵያ ህዝብ ቀምቶ መውሰዱ የአደባባይ ሚስጥር ነው።

ቢሆንም የታገለበትን አርማ የተነጠቀ ህዝብ፤ አርማውን ለመታወቂይ እና ለመፈክር ማስተጋቢያ አደረገው እናጂ፤ መራራውን ትግል የተጋፈጠው እራሱ ህዝቡ ስለሆነና ልክ ቅንጅት እንደሚለው የአርማ ስም ሁሉ ኀይሉ ሻውል የሚለውንም የቆራጥ መሪ ስም የነጻነት እና የዲሞክራሲ አጎናጻፊ አለኝታ አድርጎ በልቡ ብራና ጽፎ ትግሉን እየተፋለመ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ለፓርቲያችን በሰጣችሁት የመኢአድ አርማ ስም ስር ተሰልፎ እርሶ በቀየሱለት የአርነት ጎዳና አብሮ እስከ መጨረሻው የድል ቀን ድረስ የሚጓዝ ስለሆነ እኛም በናሽቪል ቴነሲ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ድርጅት አባላትም መኢአድ የሚለውን ስም አርማችን በማድረግ በህጋዊ መንገድ በናሽቪል የመኢአድ ድጋፍ ሰጪ ድርጅት የሚለውን ስም ፈቃድ ያወጣን መሆናችንን በከፍተኛ ደስታ ስንገልጽ መኢአድ ግፈኛውን የወያኔ አገዛዝ አስወግዶ ዲሞክራሲያዊ ስረአት ለመተካት በሚያደርገው ትግል ሁሉ ከጎኑ የተሰለፍን መሆናችንን እናረጋግጣለን።

መኢአድ የኢትዮጵያ ህዝብ አለኝታ ነው!

የፓርቲን ስም በመቀማት የህዝብ ትግል አይዳፈንም!

በናሽቪል የመኢአድ ድጋፍ ሰጪ ድርጅት ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ናሽቪል

ግልባጭ፡

ለተከበሩ ለዶ/ር ታዬ ወልደሰማያት - የመኢአድ አለም አቀፍ አማካሪ ቦርድ ሊቀመንበር
ለአቶ ግዛው ተሰፋዬ - በአሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ድርጅት ሊቀመንበር
በሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ድርጅት አመራር እና አባላት በሙሉ

Ethiopia Will Prevail!